# ሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ

## የዓለማቀፍ (ኢንተርናሽናል) መስክ ጉዞ (ፊልድ ትሪፕ) የወላጅ/አሳዳጊ ፍቃድ መስጫ ፎርም

**መመሪያዎች:**

**ለሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሰራተኞች:**
1) ለአንድ የመስክ ጉዞ አንድ ፎርም ተጠቀሙ።
2) ገጽ አንድ ላይ ያለውን ትምህርት ቤቱን የሚመለከት የፎርሙ ክፍል ሙሉት።
3) ለአንድ ተማሪ አንድ ተጨማሪ ፎቶ ኮፒ የተደረገ ቅጂ አዘጋጁ።
4) ወላጆች እና ተማሪዎች እንዲፈርሙበት አንድ ቅጂ ወደ ቤት ላኩ።
5) የጉዞው ዋና መሪ በመስክ ጉዞ ወቅት ፊርማ ያለው ዋናውን ቅጂ ከሱ ጋር ፎቶ ኮፒ ደግሞ የትምህርት ቤቱ ቢሮ ውስጥ ፋይል ላይ አኑሮ መተው አለበት።

**ተማሪዎች:**
1) ገጽ 1 ላይ የሚገኘውን "የተማሪዎች ስምምነት" ጠቅላላ ሙሉት።

**ወላጆች/ ሕጋዊ አሳዳጋዎች ተማሪው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ወይም ተማሪው ቢንያን 18 ዓመት ከሆነው፤**
1) ገጽ 2 ላይ የሚገኘውን "የአደጋ እውቅና እና የፍቃድ መስጫ" እና "የሕክምና ፍቃድ መስጫ" የሚለውን ክፍል ይምሉት።
2) ገጽ 2 ላይ የሚገኘውን "የሕክምና መረጃ" እና "የሕክምና ፍቃድ መስጫ" የሚለውን ክፍል ይምሉት።

**በትምህርት ቤቱ የሚሞላ ሚሞላ**

| | |
|---|---|
| **የትምህርት ቤት ስም:** | **የተማሪው ስም:** |
| **የመስክ ጉዞው ቀን (ቀናት):** | **የመስክ ጉዞ መድረሻ (የሚካሄድበት ቦታ):** |

**ዓላማ(ዎች):**

**የተመደቡ እንቅስቃሴዎች:**

**ቁጥጥር:** (አንዱን ይምረጡ)
_____ በዚህ የመስክ ጉዞ ወቅት በማንኛውም ግዜ ተማሪዎች በቀጥታ በአዋቂ የጉዞ መሪዎች አስፈላጊ ጥበቃ ያደረጉላቸዋል።
_____ በዚህ የመስክ ጉዞ ወቅት ቀጥሎ ከተገልጸው ሁኔታ በስተቀር ተማሪዎች በቀጥታ በአዋቂ የጉዞ መሪዎች አስፈላጊ ጥበቃ ያደረጉላቸዋል፤

**የመጓጓዣ ዓይነት:** (የሚመለከተው አንዱን ይምረጡ)

□ የትምህርት ቤት አውቶቡስ □ የከራይ አውቶቡስ □ የተመደበ የአየር መንገድ □ መርከብ /ፌሪ □ ባቡር □ ሌላ ______________________

**የተማሪዎች መነሻ ቦታ:** ______________________ **ስዓት** ______________.
**(የት)** **(ግዜ)**

**የተማሪዎች የሚመለሱበት ቦታ:** ______________________ **በግምት ሰዓት** ______________.
**(የት)** **(ግዜ)**

**ሓላፊነት ያለው/ያላቸው የጉዞ መሪዎች ስም ዝርዝር:**

**የጉዞ መሪዎች/ለተማሪ ድርሻ:** ______________________ (ቢበዛ 10 ተማሪ ለ1 የጉዞ መሪ)

**በተማሪው የሚሞላ**

### የተማሪዎች ስምምነት

በዚህ የመስክ ጉዞ በምሳረፍበት ወቅት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ እና የትምህርት ቤቴ ማህበረሰብ ወኪል እንደሆንኩ ይገባኛል። ተገቢ መመሪያዎች እና መመዘኛዎች መከብር እንዳለባቸው ይገባኛል። መልካም ስነምግባር ለመከተል ሓላፊነት እወስዳለሁ በተጨማሪም በመሰረታውያኑ የትምህርት ቤት ሕጎች እና የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መሰረታዊ ሕግ- የትከለከሉ ተግባራት/ባህሪያት ድንጋጌ መሰረት እንደምመራ ቃል እገባለሁ።

______________________ ______________________
የተማሪው ፊርማ ቀን

በወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ተማሪዎች መሞላት ያለበት

## ሊያጋጥሙ ለሚችሉ አደጋዎች እውቅና መስጫ እና የሙብት መስጫ

የእኔ/የልጄ በዚህ የመስክ ጉዞ መሳተፍ ሙሉ በሙሉ በፈቃድ መሆኑን እና መሳተፌ/መሳተፉ እኔን/ልጄን ለተወሰነ አደጋ (አደጋዎች) ሊያጋልጠን እንደሚችል ይገባኛል። ስለ መስክ ጉዞው እዚህ ፎርም ውስጥ ገጽ 1 ላይ የተሰጠውን መግለጫ አንብቤ መልእክቱ ገብቶኛል ስለሆነም እራሴን/ልጄን የተመደቡት የመስክ ጉዞው እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ/እንዲሳተፍ ፈቅጃለሁ።

ልጄ በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጥበቃ ስር በለበት ወቅት ወይም የመስክ ጉዞው ተጀምሮ እስኪያልቅ እኔ/ልጄ በዚህ የመስክ ጉዞ በምሳተፍበት/በሚሳተፍበት ወቅት ከኔ/ከልጄ መሳተፍ ጋር የተሳሰረ ወይም በኔ/በልጄ ምክንያት ሰው ላይ ወይም ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት የሆነ በቸልተኝነት ወይም በግዴለሽነት የሚፈጸም ተግባር ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ሓላፊነት እወስዳለሁ። በተጨማሪም ለጥፋቱ ለመካስ እና የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስን በሓላፊነት ላልጠይቅ፣ ከዚህ የመስክ ጉዞ ጋር በተሳሰረ ከሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጋር ግንኙነት ያለው የሆነ ግለሰብ እና ማህበራት እኔ/ልጄ በዚህ የመስክ ጉዞ በመሳተፋችን ምክንያት የሆነ የይገባኛል ጥያቄ ላላነሳ ወይም ተጠያቂ ላላደርግ ተስማምቻለሁ።

በመስክ ጉዞው መሳተፍ ከትምህርት ቤት ግቢ ውጪ እና ንብረት ሌላ በመጠቀም የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል ስለዚህ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ይሁን ሰራተኞቹ ወይም በጎ ፈቃደኞቹ ስለ ቦታው ወይም ንብረቱ ሁኔታ ይሁን አጠቃቀም የሆነ ዓይነ ሓላፊነት እንደማይወስዱ ይገባኛል/አውቃለሁ።

በመስክ ጉዞው ወቅት እኔ/ልጄ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጥበቃ ስር ከሚደርግበት እንቅስቃሴ የቀረን እንደሆነ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ለጥበቃችን ሓላፊንነት እንደማይወስድ ይገባኛል። እንደዚህ ያሉ አጋጣሚዎች እዚህ ስምምነት ስር ገጽ 14 ላይ "ጥበቃ" በሚለው ዓምድ ላይ ሰፍረዋል።

እኔ/ልጄ ይህን ጽሑፍ አንብበን እንደገባን አረጋግጣለሁ በተጨማሪም የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የተማሪዎች መብቶች እና ሓላፊነትቶች ስር የሰፈሩት መመሪያዎች እና ስምምነቶች በሚያዙት መሰረት ልንመራ እና በመማህራን፣ ሰራተኞች እና ሓላፊዎች የሚሰጥ መመሪያ እና ውሳኔዎች ልንመራ ተስማምተናል። የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ እነዚህን ሕጎች፣ መመዘኛዎች እና መመሪያዎች የማስተግበር መብት አለው። እኔ/ልጄ እነዚህን መመሪያዎች ካላከበርን ወይም በሆነ ምክንያት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሌሎችን የመስክ ጉዞ አባላት ይጠቅማል ብሎ ካመን በሆነ ግዜ ከዚህ የመስክ ጉዞ ሊከለከለን እንደሚችን እስማማለሁ በተጨማሪም እኔ/ልጄ ወደ ቤት በራሳችን ወጪ ምንም ገንዘብ ሳይመለስልን ወደ ቤት ሊመልሰን ይችላል። በተጨማሪዎ የጉዞ መሪዎች የመስክ ጉዞውን እንቅስቃሴ የግለሰቦች ወይም የጉዞ ቡድኑን ደህንነት ለመጠበቅ ሊቀይሩት ይችላሉ።

እኔ/ልጄ ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑትን ዶክመንቶች እንደ ሕጋዊ ፓስፖርት፣ ቪሳ እና ፎቶ ያለው መታወቂያ የመሳሰሉትን ማሟላት እና በጥንቃቄ መያዝ ሙሉ በሙሉ የእኔ/የልጄ  ሓላፊነት መሆኑን ይገባኛል።

## የሕክምና ፈቃድ መስጫ

እኔ/ልጄ ጤነኛ አካላዊ ይሁን አእምራዊ ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ አረጋግጣለሁ። በተጨማሪም እኔ/ልጄ ልዩ ከዚህ የመስክ ጉዞ ሊያስቀር የሚችል የጤና ወይም አካላዊ ሁኔታ እንደሌለብን አረጋግጣለሁ።

ከዚህ ፍቃድ መስጫ ጋር ተያይዘው የመጡትን "የሕክምና መረጃ ፎርም" እና "የሕክምና መፍቀጃ ፎርም" ሙሉ በሙሉ ሞልቸ ላስረክብ ተስማምቻለሁ።

እኔ/ልጄ በመስክ ጉዞ ወቅት መውሰድ የሚገባን ወይም የግድ መውሰድ ያለብን መድሃኔ ወይም/እና በሓኪም የታዘዘ መድሃኒት ካለን ለሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ማሳወቅ እንዳለብኝ ይገባኛል።

እኔ/ልጄ ላይ አደጋኛ በሽታ ወይም የመቁሰል አደጋ ካጋጠመ እና ጉዳዩ በባለ ሙያ ሓኪሞች አስተያየት የአደጋ ግዜ የሕክምና እንክብካቤ እንዲያካሄዱ ከዘዙ አስፈላጊውን ያሕክምና እርዳታ እንዲሰጡት በፊርማዬ ፍቃዴን እገልጻለሁ። በተጨማሪም የመስክ ጉዞ መሪዎች እኔን/ልጄን ወክለው እንደወላጅ ሆነው እላይ በተገለጸው የመስክ ጉዞ እንዲሳተፉ እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ወደ ሆስፒታል በሚገባበት ወይም በሚወጠበት ወቅት እኔን ወክለው እንዲሰሩ ፈቃድ እሰጣለሁ።

---

***አመካቹ ዕድሜው ቢያንስ 18 ዓመት ከሆነ የሚቀጥለው ዓረፍተ ነገር በተማሪው መነበብ እና መፈረም አለበት።***

ቢያንስ 18 ዓመት እንደሆንኩ አረጋግጣለሁ፣ እላይ ያለው ስምምነት አንብቤ ገብቶኛል የቀረቡት ሁኔታዎች እና ስምምነቶች እቀበላለሁ በሚለው መሰረትም ለስምምነቱ እገዛለሁ።

______________________________ ____________________
የተማሪው ፊርማ ቀን

***አመካቹ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ የሚቀጥለው ዓረፍተ ነገር በተማሪው ወላጆች ወይም ሕጋዊ አሳዳጊዎቹ መነበብ እና መፈረም አለበት፡***

እኔ የአመልካቹ ወላጆች እና ሕጋዊ አሳዳጊ መሆኔን አረጋግጣለሁ። እላይ ያለው ስምምነት አንብቤ ገብቶኛል የቀረቡት ሁኔታዎች እና ስምምነቶች እቀበላለሁ። ስምምነቱ በሚለው መሰረትም ለስምምነቱ በስሜ እና በልጄ ስም ተስማምቼ

ለ ______________________________ በሁሉም የመስክ ጉዞው እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፍ ፈቅጃለሁ።
(ተማሪ)

______________________________ ____________________
የወላጆች/አሳዳጊዎች ፊርማ ቀን

***ተማሪው፣ ቢያንስ 18 ዓመት በላይ ከሆነ ወይም ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች  ይህን እታች ያለውን ፎርም የግድ መሙላት አለባቸው፤***

የተማሪው ስም ከነ አባት (የሚነበብ): ______________________________

አድራሻ: ______________________________

ቴሌፎን: (ሞባይል) ____________________ (የቤት)____________________ (የስራ) ____________________

በአደጋ ግዜ ተጠያቂ ሰው ስም ከነ አባት: ______________________________

ከተማሪው ጋር ያለው ዝምድና: ______________________________

የአደጋ ግዜ ተጠሪ የስልክ ቁጥር(ቁጥሮች): ______________________________